ታደገው» አልሁ። ወዲያው ለማዕቱ አቡ ሰይፉን መጥቶ በእሳቱ ላይ ሲያማትብበት እሳቱ ጠፋ። በረድኤተ እግዚአብሔር ተደስቼ፤ ገዳሙ ከመቃጠል በመትረፉ ለፈጣሪዬ ምስጋና አቀረብሁ። የሆነውን ሁሉ ለእመምኔቷ ስነግራት፣ «ጠላት ብዙ ሙከራዎችን ቢያደርግም ጉዳት ሊያደርስብሽ ዐቅም አላገኘም፣ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው» አለችኝ።

ጠላት በአካል ገዝፎ እየመጣ መታገሉ አልሆን ሲለው፣ በረቂቅ ደግሞ ሲፈትነኝ ጀመረ። ይኸውም፦ በገዳሙ ብዙ የሥራ ኀላፊነት ስለሚሰጠኝና፣ ብዙ ጊዜዬን ከበአቴ ውጭ ማሳለፌን፣ የግል ጸሎቴን ለማድረስና ለስግደት ጊዜ ማጣቴን እያሳሰበ፤ የዚህ የዚህ እዚያው ያባቴ ቤት ይሻለኝ ነበር፣ በማሰኘት ነው። ስለዚህ ወደ ቤተሰቦቼ ብመለስ እንደሚያዋጣኝና ለመነኩሴ እንደሚገባው በጸሎት ተግቼ መኖር እንደምችል ተሰማኝ፣ ወደዚህ የመጣሁት ለጸሎት እንጂ ለአገልግሎት አልነበረም በሚል ሐሳብ ተወጠርሁ። ወደ ቤተሰቦቼ ለመመለስም ወሰንሁ። መንገዴን እንዲመራኝ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት በጠየቅሁ ጊዜ፣ አቡ ሰይፉን በሕልሜ ተገልጦ «ወደ ቤት እመለሳለሁ የምትዪው፤ ወላጆችሽ ሲሞቱ እንዴት ልታደርጊ ነው? ከገዳሙ የወጣ መነኩሴና ከባሕር የወጣ ዓሣ አንድ ናቸው። እዚሁ ቆዪ። በአገልግሎትሽ ብዛት የምታገኚው ደስታና በረከት አለሽ። ሁሌም በእንቅስቃሴሽ ሁሉ፣ ዝማሬን ከአንደበትሽ አትለዪ። ከመዝሙራት ውስጥ ልብሽን የሚማርከውንና የሚያረጋጋሽን ደግሞ በቃልሽ አጥኚው» አለኝ።

በፍቅሩ የያዘኝና የደገፈኝ አምላኬን ስለ ምክሩ አመሰግነዋለሁ። ከዚያ ቀን ወዲህ፤ ባገኘሁት ትርፍ ጊዜ ሁሉ መዝሙር ማጥናትና ውዳሴ ማርያምንም ዘወትር በኪሴ መያዝ ጀመርሁ። ምን ሥራ ቢበዛብኝና ስደክም ብውል እንኳን፤ በገነት የምኖር እስኪመስለኝ ደስ ይለኝ ጀመር።

**የመታዘዝ ፍሬ (በረከት)**፦ ትጉሕዋ የእግዚአብሔር ባርያ፣ በሙሉ ልብና በተረጋጋ መንፈስ ሆና፣ መልአካዊ ሕይወቷን ቀጠለች። የሰይጣንን ፈተናም ስለ ተለማመደችው፤ በፍርሐት ሳይሆን በትጋት መቋቋሟን ቀጠለች። ጸሎቷም በአንደኛ ተሰሎንቄ ፭፥፰ እንደ የተጻፈው፣ «የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉና፣ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና፤ እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፣ የእምነትና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር» ነው። ከአረጋውያኑም ሆነ ከወጣንያኑ መነኮሳይያት ጋር በሰላምና በፍቅር ትኖራለች። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤ በሚለው ትእዛዘ እግዚአብሔር በመመራት፣ ሁሉንም እንደራሷ ትወዳቸው ነበር። በአትሕቶ ርእስና በታዛዥነት መልካም አርአያችን ነች። እንማርበት ዘንድ፣ የልምዷን ትውስታም እንዲህ በማለት ታካፍለናለች።

በመጀመሪያው ገዳማዊ ሕይወቴ የሆነውን ልንገራችሁ አድምጡኝ ልጆቼ። አንድ ቀን በበአቴ ሳለሁ አንዲት መነኩሲት መጥታ «አንቺ ወጣኒት! ነይና በረንዳ



ውን ጥረጊ» አለችኝ። እሺ እናቴ! ብዬ ገና መጥረጊያውን ከመያዜ «ወጣኒት! ተይው በቃ» አለችኝ። እሺ እናቴ! ብዬ ተመልሼ ወደ በአቴ ገባሁ። ደቂቃ ሳትቆይ መጥታ፣ በሬን በጣም አንኳኳችና «አንቺ ወጣኒት! ነይ በረንዳውን ጥረጊ» አለችኝ። እሺ ብዬ ወጥቼ መጥረግ ስጀምር፣ መልሳ ደግሞ ተይው አለችኝ። አሁንም ቀምጬ ተመልሼ በአቴ ገባሁ። በአንድ ቀን ውስጥ፣ ጥረጊ-አትጥረጊ ስትል መጥረጊያዬን አስደጋገመችብኝ። ከዚያም ለመጨረሻ ጊዜ መጥታ «በጥሩ ቤተሰብ እጅ ማደግሽን ብዙ ጊዜ መስክረሻል። ገዳሙ፣ አንቺን ገዳማዊ ሕይወትና ሥርዓት ለማስተማር ብዙ አይጠበቅበትም» ብላ አመሰገነችኝ።

በዚህ ሁኔታ የእናታችን ትዕግሥት፣ ትሕትና፣ ታዛዥነትና ጽናት በገዳሙ እንደ መልካም መዓዛ ናኘ። ከዚህ በኋላም አመክሮዋን ስለ ፈጸመች፣ መመንኮስ የምትችል መሆኑን፤ እመምኔቷ አሳወቀቻት። በእምነታቸው የጸኑ መነኮሳት፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ስለሚያድርባቸው በሥራቸው ሁሉ ይራዳቸዋል። በዚህ ሐሴት ስለሚያደርጉ ለሚሸከሙት ቀንበር ድካም አይሰማቸውም። አገልግሎት ሲሰጡም ሆነ፤ በጸሎት ሲተጉ ያለ መታከት ነው። እግዚአብሔር በቀንም በሌሊትም ከእነርሱ ጋር ነውና፣ የተራበ አእምሯቸውንም በመንፈስ ይመግባቸዋልና፤ ጸጋቸው እየበዛ ሐሴትም እያደረጉ፤ በመጋደል የሥጋ ዕረፍታቸውን ይጠብቃሉ።[22]

**ቡሩክ ሥርዓተ ምንኩስና**፦ «ነገር ግን የባርያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዶአል። የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዷል። ይህም ነገር ምሳሌ ነው» (ኤፌ.፬፥፳፫-፬)። ፋውዚያ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ጠዋት ምንኩስና ተቀበለች። ሥርዓቱ የተፈጸመላት፣ በወጣኒነት በቆየችበት በአሮጌዋ ካይሮ በሚገኘው አ.ስ.ሴ.ገ. ነው። ያን ጊዜ፣ በገዳሙ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ባለ መኖሩ ምክንያት፤ ከገዳሙ በአፍአ በሚገኘው የአቡ ሰይፉን የሴቶች ቤተ ክርስቲያን፤ በመንፈሳዊው አባት አባ መቃርስ አል-መቃሪ እጅ ሥርዓቱ ተፈጸመላት። ስለ አፈጻጸሙ እንዲህ ብላናለች፦

በሥርዓቱ ዋዜማ ቀኑን ሙሉ ገዳሙን ስናጸዳ ዋልን። ማታ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የየግል ጸሎታችንን ስናደርስ ቆይተን፣ የሌሊት ኪዳን ጸሎት ተጀመረ። በዚያ በመጨረሻው ሰዓትም እንኳን ቢሆን፣ የተረሳ ኀጢአቷን ያስታወሰች ወጣኒት ብትኖርና መናዘዝ ቢያስፈልጋት በሚል፤ የንስሐ አባታችን ከአጠገባችን አልተለዩንም። ሥርዓተ ጸሎቱ እንደ ተፈጸመልን፤ ከአባታችን ጀምሮ እያንዳንዳቸው በዚያ የነበሩ እኅቶች፣ ዛሬ እያንዳንዳችሁ አዲስ እንደ ተወለደ ሕፃን ናችሁ። ኀጢአታችሁን ተናዛችሁና ከበደል ነጻ ሆናችሁ ለመኖር ራሳችሁን አዘጋጅታችኋልና። ይህን (የጸጋ) ልብስ የለበሰ ሁሉ የተቀደሰ ነው ይሉን ነበር።

[22] ታላቁ ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ።

